# ተጠየቅ ልጠየቅ !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

« ባ'ገር በሃይማኖት፤ በሚስት የለም ቀዛ፤
ባሞሌ አይለወጥ ባራጣ አይገዛ ! »

ብሎ የተመመው !
ባድዋ በማይጨው፤.
ለኛ ሲል የሞተው፤
ድንበር ያስከበረ - ባጥንቱ ቸንክሮ፤
ባ'ንድነት ያሰረ - በጅማቱ አክርሮ፤
ቆዳው ተፈቅፍቆ - ብራና ተሌጦ፤
ታሪኩ የተጣፈ - በደም ተበጥብጦ
ሰንደቅ የሰቀለው - ባጥንቱ ሰክቶ፤
በሥጋ ወ ደሙ - በቃል ኪዳን ጸንቶ፤
ለሰጠን አደራ ለቃል ኪዳናችን፤
ዛሬ ቢጠይቀን፤
ምንድነው መልሳችን ?!

ባሞሌ ለሸጥነው ለነፃነታችን፤
ለተቸረቸረው ለባድ መሬታችን፤
ለተሸራረፈው ያገር ድንበራችን፤
ለኛ ሲል የሞተው፤
ባድዋ በማይጨው፤.
ዛሬ ቢጠይቀን፤
ምንድነው መልሳችን?!
ለቃል ኪዳናችን መፍረስ ወይ መጠበቅ፤
መልሳችን ምንድነው ተጠየቅ ልጠየቅ?!

ቢጠይቅ ታሪኩን፤
ቢያነሳ አደራውን፤
በደም የተጣፈ ያባት ኑዛዜውን፤
ምንድነው መልሳችን ?!
ለሰጡን አደራ ማረጋገጫችን፤
ለኛነት መግለጫ የኛነት ቃላችን?!
ለቃል ኪዳናችን መፍረስ ወይ መጠበቅ፤
መልሳችን ምንድነው ተጠየቅ ልጠየቅ?!

ነሃሴ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. (August 19/2012)

ለራሴ፤ ላንተ፤ ላንቺ፤ ለሱ፤ ለሷ፤ ለኛ፤ ለነሱ፤ ለሁላችን የቀረበ ጥያቄ ::